# <u>በጸረ ወያኔነት የተሰለፈ ሁሉ ፤ የኢትዮጵያ ወዳጅ አይደለም !</u>

በሀገራችን አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር አለ ፤ ምሳሌውም እንዲህ ይላል ፤ አንዲት ሴት የሁዳዴን ጾም ስትጾም ሰንብታ ጾሙ እንደነገ ሊፈታ እንደ ዛሬ ማታ (ማለትም በዋዜማው) ዶሮዋን ለመስራት እየተንጎዳጎደች ሳለች ወጧን የሚያጣፍጥላትን ቅቤዋን ከቅቤ ቅል ውስጥ አውጥታ ወደ ወጡ ከጨመረች በኋላ በድጋሚ ከቅቤ ቅሉ ገብታ ዛቅ አደረገችና ቅቤውን ስታይ አስጎምጅቷት ኖሮ ሳታስበው ነገ ይሄን ጊዜ እያለች የጨለፈችውን ቅቤ ትልሰው ገባች ። ያ ሁሉ ጾምና ልፋት የመጨረሻው ጊዜ ሲደርስ አምሮቷን መቆጣጠር ተስኗት ድካሟን ሁሉ አፈር አስገባችው እየተባለ ይነገራል ። ይህ ምሳሌያዊ እንዲያው ለይስሙላ የተነገረ አልነበረም ።

አበው ብዙውን ጊዜ በምሳሌያዊ አነጋገር አስተምረውናል ፤ ከምሳሌው ሊያስተምሩን የፈለጉት ቁም ነገር ካመንበት አላማ በጽናት መቆም እንደሚኖርብንና የማታ ማታ ፈተናው ቢጸናም መንበርከክ እንደማይኖርብን ለማሳሰብ ነው ።

በአንድ አላማ ጸንተን ስንቆም ያ የኛ አላማ የሆነውን ደግሞ የማይስማማው በተቃራኒው የሚቆምም እንዳለ መገንዘብ ይኖርብናል ። ከኛ እምነትና አላማ በተቃራኒ የቆመው ኃይል ሁልጊዜም እምነታችን ወይም አላማችን እንዳይሳካ እንደሚፈታተነን ከማንም የተሰወረ አይደለም ። ስለሆነም እኛ ጽናታችን በጠነከረና ወደ ድል አድራጊነት በተቃረብን ቁጥር የኛ ተጻራሪ የሆነው ኃይል ካለመረታት ወይም ካለመውደቅ በስተመጨረሻው ከመረታቱ አስቀድሞ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት በመፍጨርጨር ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም ፤ ያሉትን አማራጮች ሁሉ በመዳሰስ በሚያደርገው ትግል ጽናታችንን ይፈታተናል ፤ እንደ ቆሰለ አውሬ የሚወራጨው ጠላት በሚያደርገው መንፈራገጥ በተፃራሪው ላይ አንዳንድ ጉዳት ማድረሱ አይቀርምና ያኔ ተጎንባሽ እንዳንሆን የቀደሙ አባቶች በምሳሌነት አስተምረውን አልፈዋል ።

ስለዚህ ያን ምሳሌያዊ አነጋገር በማስታወስ በጽናት መቆምና ጠንክሮ ነገሮችን መጋፈጥ ለምናደርገው የእምነት ትግል ወሳኝነት ስላለው በጽናት መቆሙ የማያጠያይቅ ጉዳይ ይሆናል ።

ዛሬም ባገራችን ሁኔታ ላይ እየታየ ያለው ይሄው ነው ። ግማሹ ጾሙን አገባዶ ሳለ ድንገት በዋዜማው ገድፏል ፤ ግማሹ ጾሙን በጽናት ቀጥሎ የፍስኩን ቀን በናፍቆት እየጠበቀው ይገኛል ማለት ነው ።

ሁላችንም እንደምናውቀው ዛሬ በተቃዋሚው ወገን የተሰለፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እከሌ ከእከሌ ሳይለይ ሁሉም ቢያንስ ሁለት አሊያም ከዚያ በላይ በሆነ ሁኔታ ተከፋፍለው ለጠላት አመቺ ሁኔታን ፈጥረውለት ለጥቃት በራቸውን ከፍተው የሽንፈት ጽዋቸውን ሲራጩ በሃዘን መመልከቱ ግድ ሆኗል ።

ከመሃከላቸውም ጽናቱን ያደለው ሽንፈትን ሳያሳይ በጥንካሬ መታገሉን ቀጥሎበት እናያለን ፤ በጽናቱ የቆመው የድል ባለቤት መሆኑ አይቀሬ ቢሆንም ፤ ሆኖም ግን ከፊቱ በጣም አሳሳቢ የሆነ ጋሬጣ እንደሚጠብቀው ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ፤ ስለሆነም ይህ ክፍል አስቀድሞ ሊዘጋጅና አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ሁሉ በተቻለ ፍጥነት ማከናወን እንደሚኖርበት የግድ ይላል ።

ወያኔ መውደቁ አይቀሬ ነው ። የመውደቁንም አይቀሬነት ነጋሪ ሳያሻው እሱ ራሱ አበጥሮ ያውቀዋል ፤ ዙሪያውን ገደል ያደረገበት እብሪቱና ማን አለብኝነት እንደሆነ ግን የተረዳው አይመስልም ። ሆኖም ግን እንደኔ “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው” ስለሆነ ወያኔ በራሱ ጥፋት ይውደቅ ወይም ሌላ ኃይል ይጣለው ዋናው የወያኔ መውደቁ እስከሆነ ድረስ በጸጋ የምቀበለው ሆኖ ሳለ ነገር ግን ያሉት ተቃዋሚ ነን ባዮችን አቋምና አመለካከት ሳየው ዞሮ ከጭንቀትና ከሃሳብ አያወጣኝም ።

የወያኔ የመወገድ ጉዳይ ግን ወደድንም ጠላንም አለመስዋትነት እንደማይሆን አስቀድመን መገንዘብ ይኖርብናል ። መስዋዕትነቱ ምን ያህል ይሆናል? እሱ በጽናት የቆመው ክፍል በሚያደርገው ጥረት ስለሚመዘን ለመተንበይ ይቸግራል ።

ወያኔ ለሕዝብና ለሐገር ያለው ንቀት ከቀን ወደ ቀን እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም ። በመሆኑም ዛሬ በተቃዋሚ ድርጅቶች ፤ በሚዲያዎችና በመሳሰሉት ላይ የሚያደርሰውን አፈና ፤ እስራትና ግድያ እያጠናከረው ሄዷል።

አብሪተኛው ወያኔ ኤርትራንና የአሰብን ወደብ አሳልፎ የሰጠው አልበቃ ብሎት ዛሬም ሕዝብንና አገርን ከመናቁ የተነሳ በማን አለብኝነት ተነሳስቶ አገር እየሸነሸነና እየመተረ መቸብቸቡን በሰፊው ተያይዞት ይታያል ። ሰፊና ትልቁን መሬት ቆርሶ ለሱዳን የሰጠ ሲሆን ፤ በመቀጠልም ለጅቡቲና ለሳውዲ አረቢያ መንግሥታት ሰፋፊ መሬቶችን አለከልካይ ለመሸጥ በቅቷል ። ይህንን ወርቃማ አጋጣሚ እንዳያመልጣቸውም የኬኒያ ፤ ቡርኪናፋሶ ፤ ማሌዢያና ሌሎችም አገሮች ድርሻቸውን ለማግኘት ተራ በመጠበቅ ላይ እንደሆኑም መገመት አያዳግትም ።

ይህን አይነት በዓለም ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ፤ በአይነቱ ልዩና የመጀመሪያ የሆነው አብሪተኛው ወያኔን ከሌሎች አምባ ገነን መንግሥታት ልዩ የሚያደርገው ፤ አምባ ገነኖች በተፈጥሮ ጸረ ሕዝብና አፋኝ ቢሆኑም ግዛት ለማስፋፋት ግን ጽኑ ምኞት ስላላቸው ባብዛኛው ግዛታቸውን ለማስፋፋት ሲሉ ብዙ አላስፈላጊ ጦርነቶችን እንደሚያጭሩ ነው ። የኛው አምባ ገነኑ ወያኔ ግን በተቃራኒው የገዛ አገሩን ሸንሽኖ በመቸርቸር ፤ በሃራጅ እያወጣ በመሸጥ በአይነቱ ልዩና የመጀመሪያው አምባ ገነን ያደርገዋል ።

ታዲያ ይህ ሁሉ ወንጀል በሚፈጸምባት አገራችን ዛሬ ይባስ ብሎ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረው ሕዝባችን በርሃብ አለንጋ እየተገረፈ ይገኛል ። የኑሮ ውድነቱም ከሚገባው በላይ በመናሩ ጥሩ ኑሮ የሚኖሩ ተብሎ የሚነገርላቸው የከተማ ነዋሪ የሆኑና ካብዛኛው ኢትዮጵያዊ የተሻለ ገቢ ያላቸው እንኳን እራሳቸውንም ሆነ ልጆቻቸውንም መመገብ የማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል ።

ዛሬ ባገራችን ባብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ በጠፋበት ወቅት በውስኪና በኮኛክ እየተራጨ ጮማ የሚቆርጠውና ከጥጋብ በላይ በቁንጣን እየተሰቃየ ያለው ወያኔና የወያኔ ግብራበር የሆኑ በንግዱም ሆነ በፖለቲካው ፤ እንዲሁም በመንግሥት መዋቅር የታቀፉ ጥቂት የአምባ ገነኑ ታማኝ ቡችሎች ብቻ ናቸው ።

ይህ አይነት ሁኔታ ለጊዜው በትዕግስት የታለፈ መስሎ ቢታይም ፤ ውስጥ ውስጡን በቁጭትና በንዴት የሚብላላው ሕዝባችን ረሃቡና ችግሩን ከማይታገስበት አንድ የተወሰነ ደረጃ ሲደርስ አለማንም አነሳሽነትና አደራጅነት ሕዝብ እራሱ በራሱ በግብታዊነት ለአመጽ መነሳቱ  አይቀሬ ይሆናል ።

ይህ የሕዝብ አመጽ የረጅም ጊዜ ቁጭትና ንዴትን ያዘለ በመሆኑ በቀላሉ የሚገታ አይሆንም ፤ በወያኔ የግፍ ጭፍጨፋም የማያፈገፍግና ወደኋላ የማይል እንደሚሆን ለመናገር ነብይነትን አይጠይቅም ። ስለሆነም ወያኔን ለማዳን ፤ አጋዚም  ፤ የአፋኝ ድርጅቱም ሆነ ሰራዊቱ ከሕዝብ ቁጣ ሊያስጥሉት በማይችሉበት ወቅት ፤ ሁኔታዎች ሁሉ ከቁጥጥር ውጪ ሲሆኑ ፤ ያኔ ወያኔ ቢችል ትግራይን ገንጥሎ ለመሄድ ፤ ካልሆነም እግሬ አውጪን ብሎ በዘረፋ ያካበተውን ሀብት እየበላ ለመኖር ወደምዕራቡ አለም በጥገኝነት ለመኖር አገሪቱን ወደማትወጣው ድህነትና ትርምስ ውስጥ ጥሎ እንደሚፈረጥጥ ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

በቁጭትና በንዴት አለ ፖለቲካ ፓርቲ አደራጅነት የተነሳሳው ሕዝባዊ አመጽ ከዚህ ቀደም እንዳየነው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ተነሳስቶ የንጉሱን ሥርአት ከስር መሰረቱ ከገረሰሰው በኋላ ሕዝቡ  ባለመደራጀቱና በሕዝቡንም ያቀፈ የፖለቲካ ድርጅት ባለመኖሩ ይነስም ይብዛም በመደራጀት መልክ የነበረው የጦር ሰራዊቱ ብቻ ስለነበረ ያ ሕዝባዊ ድል በመለዮ ለባሹ በቀላሉ ሊቀማ ችሏል ።

ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ ዛሬም የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ አሸን የፈሉ ቢሆኑም ፤ እርስ በርሳቸው ቅራኔ ያላቸውና በውስጣቸውም ያን ያክል የሚያኮራ የሕዝብ አመኔታና ድጋፍ ያላቸው ስላልሆኑ አሁንም ሕዝብ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ያመጣው ለውጥ በቀላሉ በመለዮ ለባሹ የማይቀማበት ምክንያት አይታየኝም ።

ሆኖም ግን ሕዝባችን ካለፈው ወታደራዊ መንግሥት ያካበተው የደለበ ተመክሮ ስላለው ለመለዮ ለባሹም እንደ ደርጉ ዘመነ መንግሥት ቀላል የሽግግር መንግሥት ሊሆንለት እንደማይችል ማስላት አያዳግትም ።

ወያኔን በትክክለኛው መንገድ እየተቃወሙ ሕዝባዊና ሐገራዊ መንግሥት ለመገንባት የሚታገሉ ድርጅቶች ያለው የወታደርና የጸጥታ ኃይል የሕዝብ ወገን እንዲሆን ካሁኑ መሰረታዊ የድርጅት መዋቅርን መጣል ከወያኔ (TPLF) መገንጠልና ሕዝባዊ እንዲሆን ያልተቆጠበ ቅስቀሳ ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

ይህ በተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ብቻ የሚጣል ሀላፊነት ብቻ ሳይሆን ሀላፊነቱ ማንኛውንም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሚመለከተውና ሀላፊነቱም የኔም ጉዳይ ነው ብሎ ሊሰራበት የሚገባው ጥያቄ ነው ፤ ይህ እስካልሆነ ድረስ ወያኔ በግብታዊነትም ይውደቅ በተደራጀ መልክ የጦር ኃይሉ እንደ (Institute) በሐገሪቱ የስልጣን የመያዝ ሁኔታን በተመለከተ ከታሪክም እንደተገነዘብነው አሁንም ስልጣኑን ከህዝብ ለመንጠቅ ወደኋላ አይልም ። ለጊዜው ባግባቡ ተደራጅቶ የሚገኘው ኃይል እሱው ነውና ።

ይህንን መሰል መናጋት በሚፈጠርበት ወቅት ስርአተ አልበኝነት ይነግሳል ፤ ይህንን አጋጣሚም በመጠቀም በጎጠኝነትና በግንጠላ ናፍቆት ናላቸው የዞረ ጠባብ ብሄርተኞችም (BINGO) ለማለትና የከረመ ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ወደኋላ እንደማይሉ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ በመሆኑ ፤ ምናልባትም የፈለግነውን ማግኘት ቀርቶ ወዳልፈለግነውን የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እንዳንማገድ ያስፈራኛል።

ከላይ የዘረዘርኳቸው ሊሆኑ ይችላሉ ያልኳቸውን ሁሉ እንዳይፈጠሩ ማድረግ ሲቻል ፤ ሆኖም ግን በስመ ጸረ ወያኔ ተደራጀን የሚሉ ነገር ግን ከሐገርና ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የራሳቸው የስልጣን ናፍቆት የሚወዘውዛቸው ፤ በነ መለስና በረከት ወንበር ተቀምጦ ቂጣቸውን ለማሸት የቋመጡ አስመሳይ ታጋዮች ፤ ሐገራችን ከወያኔ ባሻገር ብሩህ ተስፋ እንዳይኖራት ደፋ ቀና እያሉ ሲዋትቱ ማየት ካማሳዘን በላይ በቃላት የማይገለጽ አልህና ንዴትን እያጫረብኝ መጥቷል ።

ዛሬ ሁላችንም በግልጽ እንደምናውቀው ኦነግና ፤ ኦብነግ ኢትዮጵያዊ ነትን ያልተቀበሉ ፤ እንዲያውም በጸረ ኢትዮጵያ አቋም የተሰለፉ ፤ አገራችንን ለማፈራረስና ለመበታተን በምዕራባውያን ፤ በአረቦችና በሻቢያ እየታገዙ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው እየታወቀ የኛዎቹ ተቃዋሚ ነን ባዮችም አርጩሜ ሳይኖራቸው ለግንጠላ በተሰለፈና እስከ አፍንጫው ድረስ ከታጠቀ ቡድን ጋር በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ አብሮ መስራት ይቻላል እያሉ ከስራቸው ተንበርክከው ጭራቸውን ሲቆሉ መመልከት ምን ሊያስኛቸው እንደሚችል አላውቅም ። በመሰረቱ ወደ ኢትዮጵያዊነት የመጣና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታገል ማንኛውም ድርጅት በቅድሚያ ሊያሰምርበት የሚገባ ጉዳይ  ቢኖር በማያሻማ ሁኔታ <u>“ኢትዮጵያዊነትን ማመንና መቀበል”</u> ነው ። ይህ በሌለበት ቦታ አብሮ መስራት ማለት በራስ ከማሾፍ የተለየ አይሆንም ። ኢትዮጵያዊነትን ግን በማያሻማ ሁኔታ ከተቀበሉ ከዚያ በኋላ የሚቀጥለው ሁሉ እዳው ገብስ ነው ።

ነገር ግን ይህ ቅድመ ሁኔታ ባልተሟላበት በአሁኑ ወቅት እነዚህን ጸረ ኢትዮጵያ ድርጅቶችን አቅፎ መጓዝ ኢትዮጵያዊነት ሳይሆን ጸረ ኢትዮጵያዊነት እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል ።

ገና ለገና ደጋፊ ያበዙ መስኳቸው ወያኔ ሊወድቅ በሚንገዳገድበት በአስራ አንደኛው ሰዓት ላይ በስመ ታጋይ የተሰለፉ ገሚሱ ቀድሞም ጽናት ባለፈበት ያላለፉ መሆኑ እየታወቀ ፤ አንዳንዱ ከላይ እንደተጠቀሰው ምሳሌያዊ አነጋገር ከአርባ አመት ጾም በኋላ ተስፋ ቆርጦና ተረትቶ ፤ ጸንቶ የቆየበትን የእምነት ማተቡን በጥሶ ፤ ከጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ተሰልፎ በዓላማቸው የጸኑትንና ያልተንበረከኩትን ንጹህ የኢትዮጵያ ልጆችና ድርጅቶችን በማጣጣልና መወንጀል በደካማ አመለካከቱ ተሸብቦ ተይዞ እራሱን ያጎለበተ መስሎት መኮነኑንና ሥም ማጥፋቱን ሥራዬ ብሎ ተያይዞት ባለበት ወቅት ፤ እውን እነዚህ ቡድኖች ከየትኛው ወገን ናቸው የሚል ጥያቄ በሁላችንም ህሊና ማጫሩ አልቀረም ።

ከነዚህም አጋዥና አጋፋሪ በመሆን የሚሰሩ የውጪው ኑሮ የከበዳቸውና የሰለቻቸው  በሐገሩ ደሃ ሕዝብ ጫንቃ ተቀምጦ ለመሸምና ለመብላት ያደገደገ ምሁራን ተብዬዎች ሲያጋፍሩ ማየት የተለመደ ትያትር ሆኗል ።

በቅዠት አለም ለሚዋዥቁ ምሁራንም ሆነ በተቃዋሚ ሥም እየሰራን ነው ለሚሉ ሁሉ ግን አንድ በጣም ሊሰሙት የማይፈልጉት ነገር ግን ልነግራቸው የተገደድኩበት ጉዳይ አለ ። መርዶ ነጋሪ በመሆኔ ግን እጅግ ማዘኔን ከተቡልኝ ።

ነገሩ እንዲህ ነው አንድ የሩቅ ዘመዴ የሚሆን ሰሞኑን አገር ቤት ደውዬ ስለ ሐገራችን ሁኔታ በሰፊው ከተጨዋወትን በኋላ ሕዝቡ እዚህ በውጪ አገር እየተንቀሳቀስን ነው ስለሚሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ያለውን ግንዛቤና ሕዝቡ ለነሱ ያለውን ድጋፍ እንዲነግረኝ ጠይቄ ያገኘሁት መልስ እንዲህ የሚል ነበር ።

ባይገርምህ እኛ ይኑሩም አይኑሩም የምናውቀው ነገር የለም ። እኛ የምናውቀው እዚሁ ከኛ ጋር አብረው እየታገሉ ፤ እንደኛው እየታሰሩ ፤ እንደኛው እየተገርፉ ፤ እንደኛው እየተገደሉ ያሉትን እንጂ አውሮፓና አሜሪካ በድሎት ተቀምጦ እኛ በሞትነውና እኛ በተፈተንበት በሚገኝ ለውጥ ላይ ያገባናል ፤ እናዛለን ፤ ብሎ የሚመጣ የሩቅ ሰው ተቀባይነት የለውም ሲል ፍርጥም ባለ አነጋገር አስቀምጦታል ።

እንዲያውም አዲስ ሥም ወጥቶላቸዋል “ማርሻን” ነው የሚባሉት አለኝ ፤ ለመሆኑ ማርሻን ማለት ምን ማለት ነው ብዬ ስጠይቀው ፤ በአይን ያላየናቸው ፤ በእጅ ያልዳሰስናቸው ባፈ ታሪክ ብቻ የምናውቃቸው ፤ በሳይንሱና በቴክኖሎጂው ከሰው ልጅ እጅግ የረቀቁ ሆነው በግምት በአሜሪካን የፊልም ኩባንያዎች የሚቀርቡልን የማርስ ሰዎች ማለት ነው አለኝ ፤  ሰው ዛሬ ወሬ ሲያበዛና አንጀት ጠብ የማይል ነገር ሲዘባርቅ ባክህ ማርሻን አትሁን ነው የሚለው በማለት አስቆኛል ።

ከዚህ ሆነው ዛራም ይመስል የሚያጓሩብን ሁሉ በኢትዮጵያዊው ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው ስሰማ ሕዝቡ ምን ያህል እዚህ ካለነው በላይ የነቃ እንደሆነ ለማወቅ አስችሎኛል ። እንዲያውም ተከፋፍለው እንዲህ ሆነ ፤ እንዲያ ሆነ ፤ እየተባለ ስንሰማ በድንቁርናቸው እንስቃለን ብሎኝ አረፈው ። እንግዲህ እነ ማርሻን በጥሞና እርማችሁን ልታወጡ ይገባልና አስቡበት ።

ታዲያ ዛሬ አገር ቤት ያለው ሕዝባችን ምን ማድረግና ምን መደረግ እንዳለበት ጠንቅቆ እያወቀ ሳለ ፤ እኛ ከብዙ ሺህ ማይል አርቀት ተቀምጠን እናውቅልሀለን ማለት በእውነት ያሳፍርም?

ሕዝባችን የሚያውቀውን ያውቃል ፤ ሊነግረን የሚያስፈልገውን ነግሮናል ፤ ያም ሆኖ ግን ቅንነትን በተመረኮዘ መልኩ ትግሉን እናግዛለን ካልን በስርአት ተደራጅቶ በስርአት መታገል ሲገባ ፤ በስመ ወያኔን ተቃዋሚ ተብሎ ጸረ ሕዝብና ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ አሰስ ገሰሱን እያግበሰበሱ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ወኔን ሰልቦ ለሰካቢ መስጠት ፤ የጽናትን መሰረቱን ለማናጋት መሞከር ፤ ትግል እያሉ ትግልን መግደል ፤ ተገቢ አይደለም ፤ በጸረ ወያኔነት የተሰለፈ ሁሉ የኢትዮጵያ ወዳጅ አይደለምና ሊታሰብበት ይገባል ። ሕዝባችንም ሲናገር ሊደመጥና ቃሉም ሊከበር እንደሚገባ እያወቅን ፤ የእናውቅልሃለን ፖለቲካ ወንዝ አያሻግር ተገንዝባችሁ  ማርሻኖች ነገሩን በጽሞና ብታስቡበት መልካም ነው በማለት ወንድማዊ ምክሬን ሳልለግሳችሁ አላልፍም ።

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ! !

ከአይምሮ ዳኛቸው